# ‘‘የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበር’’

## መተዳደሪያ ደንብ

የካቲት 05/2002 ዓ.ም

# የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበር
# የመተዳደሪያ ደንብ

## አንቀፅ 1፡- መቋቋም

የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበር የተባለ ማህበር በ 25 ቀን በህዳር ወር 1989 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡

## አንቀፅ 2፡- ስያሜ

የማህበሩ ስም "የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበር" ሲሆን፣ በአጭሩ ሲፃፍ "ኢቴባማ" ይባላል፡፡

የማህበሩ ስም በእንግሊዘኛ ሲፃፍ "Ethiopian Information Technology Professionals Association"ሲሆን፣ በአጭሩ ሲፃፍ "EITPA"_ይባላል፡፡

## አንቀፅ 3፡- ዓላማ

1. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ በአባላቱ ተሳትፎ እንዲዳብር ማድረግ
2. የአባላቱ የሙያ ጥቅም ማስከበርና ሙያዊ ክህሎት እንዲዳብር ማድረግ
3. የኢጥዮጵያ የትምህርት ተቋማት፣ የኢንፎርሜሽን ማቀነባበሪያ ማዕከላት፣ አጠቃቀም ላይ አባላቱ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያግዛል ያበረታታል
4. በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስክ አባላቱ ምርምር እንዲካሄድና ውጤቱም በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራጭ እገዛ ማድረግ፡
5. ከሙያው ጋር ዝምድና ለለቸው ሃሳቦች አመለካከቶች ለአባላቱ የውይይት መድረክ መፍጠር

## አንቀፅ 4፡- የበጀት አመት

የማህተሩ የመጀት አመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 5፡- ትርጉም

1. "ማህበር" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበር ነው፡፡

2. ”ኤጀንሲ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው፡፡

3. ”ጠቅላላ ጉባኤ” ማለት መስራች አባላትና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡

## አንቀፅ 6፡- አባላት

ማህተሩ አራት የአባልነት ምድቦች ይኖሩታል፡፡ እነሱም መደበኛ አባላት፣ ተባባሪ አባላት፣ የድርጅት አበላት እና የተማሪ አባላት ናቸው፡፡

**1.መደበኛ አባላት**

ሀ. መደበኛ አባል ለመሆን፣ ከሚከተሉት መመዘኛዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ ኢትዮጵያውያን አባል መሆን ይችላሉ፡፡

- በኮምፒውተር ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንፎርሜሽን ሳይንስ ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተመሳሳይ መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ እና አዛበላይ ያላቸው፣ ወይም
- የዩንቨርስቲ ዲግሪ ያላቸውና በኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ፣ በሲስተምስ አናሊሲስ ወይም በኢንጅነሪንግ የ1 አመት የስራ ልምድ ያላቸው፣
- በኮምፒውተር የትምህርት መስክ፣ በኮምፒውተር ኢንጅነሪንግ፣ ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዲፕሎማ ያላቸው፣ ወይም
- የዩንቨርስቲ ዲፕሎማ ያላቸውና በኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ፣ በሲስተም አናሊሲስ ወይም በኢንጅነሪንግ የ5 አመት የስራ ልምድ ያላቸው፣

ለ. አባላት የመመዝገቢያ ብር 10.00 እና አመታዊ የአባልነት መዋጮ ብር 48.00 ይከፍላሉ

**2.ተባባሪ አባላት**

ሀ. ተባባሪ አባላት ለመሆን፣ የኮምፒውተር ተጠቃሚ የሆኑና የኮምፒውተር እውቀታቸውን ማስመስከር የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ይችላሉ፡፡

ለ. በተባባሪ አባልነት ቢያንስ ለ3 ዓመታት በንቃት ከተሳተፉ ለመከነኛ አባልነት ማመልከት ይችላሉ፡፡

ሐ. ተባባሪ አባላት የመመዝገቢያ ብር 15.00 እና አመታዊ የተባባሪ አባልነት መዋጮ ብር 9.00 ይከፍላሉ፡፡

3. የድርጅት አባላት

ሀ. የድርጅት አባል ለመሆን፣ የማህበሩን ዓላማ የሚደግፉ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ድርጅቶችና ተቋሞች ይችላሉ፡፡

ለ. የድርጅት አባላት የመመዝገቢያ ብር 200.00 እና አመታዊ የድርጅት አባልነት መዋጮ ብር 500.00 ይከርላሉ፡፡

4. የተማሪ አባላት

ሀ. የተማሪ አባል ለመሆን፣ የማህበሩን አላማ የሚደግፍ በኮምፒውተር ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንፎርሜሽን ሳይንስ ወይንም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተመሳሳይ መስክ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ለ. የተማሪ አባላት የመመዝገቢያ ብር 2.00 እና አመታዊ የተማሪ አባላት መዎጮ ብር 5.00 ይከፍላሉ፡፡

## አንቀፅ 7፡- የክበር አባላት

1. የማህበሩ አባል ያልሆኑና የማህበሩን ዓላማ ለማስፈፀም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ፣ ማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ፡፡
2. የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባላት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም፡፡

## አንቀፅ 8፡- የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው፡፡ ሆኖም፣ ተባባሪ አባላት፣ የድርጅት አባላት፣ የተማሪ አባላት እና የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም
2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው፡፡
3. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል፡-

ሀ. ለማህበሩ አላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፤

ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣ እና

ሐ. በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና እምፅ የመስጠት መብት አለው/አላት።

መ. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በስታ አስፈፃሚ ቦርድ የመሰማት መብት አለው።

## አንቀፅ9፡- የአባላት ግዴታ

1 ማንኛውም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ የመክፈል አለበት/አለባት፤

2 አንድ አባል ከአባልነት የመሰናበቱ/ቷ የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ መክፈል ይኖርበታል/ይኖርባታል፤

3 ማንኛውም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማክበር አለበት/አለባባት፤

4 ማንኛውም አባል የማህበሩን አላማና የገባቸውን/የገባችውን ግዴታዎች ማክበር፣ የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት/አለባት፤

5 በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት።

## አንቀፅ 10፡- የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን ማሻሻል ሲያስፈልግ በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል።
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል አባል በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጫ ይጣልበታል/ይጣልባታል።
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት አይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሲያነሳ ይችላል።

## አንቀፅ 11፡- አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው፡-

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሰረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
4. ለማህበሩ አላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸው በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ ጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣
6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣
7. ከማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በፅሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

## አንቀፅ 12፡- የማህበሩ አደረጃጀት

1. ማህበሩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ

   ለ. ኦዲተር

   ሐ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

   መ. የክልል ተወካይ እና

   ሠ. ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

2. ማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው፡-




3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

## አንቀፅ 13፡- የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣
   - ለ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ያሻሽላል፣
   - ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣
   - መ. የቦርድ አባላትን፣የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊ ይሾማል ይሽራል፣
   - ሠ. የማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎችን የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   - ረ. ማህበሩን መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣
   - ሰ. የማህበሩን አመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና አመታዊ በጀት ያፀድቃል፣
   - ሸ. አመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   - ቀ. በማኅበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳይ ላይ ይወስናል፣
   - በ. በማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

ኀ. የማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

ኘ. ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውጣኔ ይሠጣል፡፡

አ. በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ)፣(በ)፣(ቸ) እና (ኀ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ አመራር አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

<u>አንቀፅ 14፡- የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል፡
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ስርአት ፍትሃዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
5. ከጠቅላላ ጉባኤ የተለየ ሃሳብ ያለው/ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች፡፡
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤ የተላለፈው ውሳኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይሰጣል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች፡፡

## አንቀፅ 15:- የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሃፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

**1.የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ፣**

ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከፀሃፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦች የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

መ. ጉባኤው ያፀደቃቸው አመታዊ የስራ ክንውን፤ የስራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሃፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣

**2. ምክትል ሰብሳቢ**

ሀ. ሰብሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሰራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

**3. ፀሃፊ**

ሀ.ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፤

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

## አንቀፅ 16: የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው በደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት አመቱ ከተዘጋ በኂላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያለጠራ እንደሆን ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚህ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረትር ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. የማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡
5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት አስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ቦታውን፣ ቀኑን፤ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡
6. የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
7. በዚህ በላይ በንኡስ አንቀፅ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልአተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡
8. ጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሃፊ/ ሊቀመንበር/ ፕሬዝደንት / የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/ በፅሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡

## <u>አንቀፅ 17፡ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወስኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈፅማል፣
4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምፅ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን/4 ዓመት/ ማረፍ ይኖርባቸዋል፡፡

6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
7. የማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በእጩነት ማቅረብ አይችሉም።ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት ለእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ እለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልፀደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

## <u>አንቀፅ 18፡- የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባራት</u>

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ሆኖ የማህበሩን የእለት ተእለት ስራ ያከናውናል።
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
   ሀ. የማህበሩን አመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣
   ለ. የማህበሩን አመታዊ የስራ መርሃ ግብርና የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣
   ሐ. የማህበሩን አላማዎች ለማስፈፀም የገቢ ምንጮችን የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፣
   መ. የማህበሩን ፖሊሲን በማመንጨት ያቀርባል፣
   ሠ. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣ዝውውር፣ እድገት፣ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል።
   ረ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፍ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።
   ሰ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል።

ሸ. የአባልነት ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሓሳብ ያቀርባል፡፡

ቀ. የራሱን የአሰራር ስነስርአት ያወጣል፡፡

በ. በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

ተ. የማህበሩን መደበኛ አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፡፡

## አንቀፅ 19፡- የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

1. የስራ አመራር ቦርድ 7 አባላት ይኖሩታል፣(ቢሆንም የቦርዱ ቁጥር ለውሣኔ አሰጣጥ እንዲያመች ጎዶሎ መሆን ይኖርበታል)
2. ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ.ፕሬዝዳንት

   ለ. ምክትል ፕሬዝዳንት

   ሐ. ፀሃፊ

   መ. ሂሳብ ሹም

   ሠ. ገንዘብ ያዥ እና

   ረ. ሌሎች ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡
3. **ፕሬዝዳንቱ/ቷ፤**

   ጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉት ስራዎችን ያከናውናል፡፡

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቋቁማቸው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

   ለ. ማህበሩን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

   ሐ. በማህበሩ ስም የተከፈለው የባንክ ሂሳብ ቼኮችንና የወጪ ሰነዶችን ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፡፡

   መ. ለማህበሩ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይፈቅዳል፡፡

   ሠ. የ3ወር፣ የ6ወርና አመታዊ የስራ፣ የፋይናንስ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

   ረ. በማህበሩ ስም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

   ሰ. ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዡን ጨምሮ በስሩ የሚገኙትን ሰራተኞች እያስተባበረ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማህበሩን የእለት ከእለት ስራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

ሸ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በማስፈቀድ በማህበሩ ስም ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ ውሎችን ያዋውላል፡፡

ቀ. በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፍ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላል፡፡

በ. ሌሎች ለስራ አስፈፃሚው የሚሰጠውን ስራ ያከናውናል፡፡

ተ. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ካልተሾመ ወይም ከሌለ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ሆኖ ይሰራል፡፡

4. **ምክትል ፕሬዝዳንቱ/ቷ፡**

ሀ. ፕሬዝዳንቱ/ቷ በማይኖሩበር ጊዜ ፕሬዝዳንቱን/ቷን ተክቶይሰራል፣

ለ. በፕሬዝዳንቱ/ቷ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ስራ ያከናውናል፡፡

5. **ፀሃፊ**

ሀ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሃፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ለ. ከስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የማህበሩን የመፃፃፍ ግንኙነት ስራዎች ያከናውናል፡፡

ሐ. የስራ አስፈፃሚውን አጀንዳ ያዘጋጃል ቃለጉባኤ ይይዛል፡፡

መ. የማህበሩን ማህተም፣ ሰነድና መዛግብት ይይዛል፡፡

ሠ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡

ረ. የጠቅላላ ጉባኤው ፀሃፊ ካልተሾመ ወይም ከሌለ የጠቅላላ ጉባኤው ፀሃፊ ሆኖ ይሰራል፡፡

6. **ሂሳብ ሹም**

ሀ. የማህበሩን ገቢና ወጪ ሂሳብ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

ለ. የማህበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሰራር ደንብ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሐ. በማህበሩ ስም የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ቼክና የወጪ ሰነዶች ላይ ከፕሬዝዳንቱ ጋር ወይም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. የማህበሩ የሂሳብ መዛግብት በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

ሠ. የሂሳብ መዝገብ፣ ገቢና ወጪ፣ ሃብትና እዳ ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ረ. ማህበሩ ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ስራ የሚውሉ የተለያዩ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

7. የማህበሩ ገንዘብ ያዥ

ሀ. የማህበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣

ለ. የተሰበሰበውን ገንዘብ ሃገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

ሐ. ለስራ ማስኬጃና ለማህበሩ ይቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000.00(ብር አስር ሺህ) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣

መ. ከሂሳብ ሹሙ ጋር የገቢና የወጪ ሂሳብ በየወሩ ያመሳክራል፡

ሠ. የማህበሩን ቼክ ይይዛል፣

ረ. በጣምራ ፊርማ/ በሂሳብ ሹሙና በስራ አስኪያጁ/ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 20፡- የስራ አመራር ኮሚቴ የስብሰባ፣ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን

1. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በአመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዝዳንቱ ወይም በምክትል ፕሬዝዳንቱ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልአተ ጉባኤ ከተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልአተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙት አባላት ስብሰባ ሊዳሄድ ይችላል፣
4. ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይፀናል፣
5. የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አንድ የኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣
6. የኮሚቴ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ሆኖም ለማህበሩ ስራ ለሚወጡት ወጪዎች ማካካሻ ወይም አበል በጠቅላላ ጉባኤው ፀድቆ ሊከፈል ይችላል፡፡

## አንቀፅ 21፡- የኦዲተር ሃላፊነትና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩን ኦዲተር በኤጀንሲው ተቀባይነት ባለው የኦዲት ቢሮ ቀጥሮ መተካትና ኦዲቱን ማሰራት ይችላል፡፡
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡
3. የማህበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል

4. የማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
5. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት አመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል

## አንቀፅ 22፡- የክልል ተወካይ ሃላፊነትና ተግባር

1. የማህበሩ አላማና እንቅስቃሴ በተወከለበት/በተወከለችበት ክልል ማሳወቅና እንዲስፋፋ ማድረግ
2. በክልሉ/ሏ ሊሰሩ ወይም ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማውጣት የአፈፃፀም እቅድ ለማህበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ማቅረብ
3. በክልሉ/ሏ የሚገኙትን የማህበሩን አባላት መሰብሰብና ማወያየት
4. ማህበሩ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴ በተመሳሳይ በክልሉ/ሏ መተግበር

## አንቀፅ 23፡- የማህበሩ የገቢ ምንጭ

የማህበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከህዝባዊ መዋጮ፤ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 24፡- የማህበሩን መተዳተሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሃሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሃሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፤ ጸሃፊ ወይም ፕሬዝዳንት የጉባኤ ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሃሳብ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ 3/4ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው፡፡
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ኤጀንሲው ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡

## አንቀፅ 25፡- ስለማህበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. ማህበሩ ወደተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስን ነው፡፡
2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማህበር ጋር የሚያደርገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ፀሃፊና የማህበሩን ፕሬዝዳንት ማካተት ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 26፡- ስለማህበሩ መፍረስ

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ፕሬዝዳንት የንብረት ዝርዝር (Inventory) አዘጋጅቶ ከማፍረስ ስሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

## አንቀፅ 27፡- የመተዳደሪያ ደንብ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ከፀደቀበት ከየካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡